# በደብረሰላም፡ መድኃኔዓለም፡ የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋህዶ፡ ቤተክርስቲያን



**የመድኃኔዓለም፡ የጽዋ፡ ማህበር፡ መተዳደሪያ፡ ደንብ**

**ሚኒሶታ**

**ኅዳር፡28, 2007 ዓም/ December 7, 2014**

# መግቢያ፡

## የመድኃኔዓለም፡ የጽዋ፡ ማህበር፡ በሚኒሶታ

አባቶቻችን፡ ሊቃውንተ፡ ቤተክርስቲያን፡ እንደሚተርኩት፡ ማህበር፡ የሚለው፡ ቃል፡ ሲተረጎም፡ በአንድነት፡ በመተባበር፡ መኖር፡ ማለት፡ ሲሆን፡ ቃሉ፡ የግዕዝ፡ ቃል፡ መሆኑን፡ ይነግሩናል። በማያያዝም፡ በምድራዊው፡ ዓለም፡ በማህበር፡ ወይም፡ በመተባበር፡ መኖር፡ የተጀመረው፡ ከቀዳሚዎቹ፡ ፍጥረታት፡ ከአባታችን፡ ከአዳምና፡ ከእናታችን፡ ከሔዋን፡ ጊዜ፡ ጀምሮ፡ እንደሆነ፡ እና፡ ከዚያም፡ በኋላ፡ ልጆቻቸውና፡ የልጅ፡ ልጆቻቸው፡ አሁን፡ እኛ፡ እስካለንበት፡ ዘመን፡ ድረስ፡ በተለያየ፡ መልኩ፡ ሲጠቀሙበት፡ እንደቆዩ፡ እና፡አሁንም፡ እየተጠቀሙበት፡ መሆኑን፡ ለቃውንተ፡ ቤተክርስቲያን፡ በሰፊው፡ ያስረዳሉ። እንዲሁም፡ ማህበር፡ ከምድራዊ፡ ሰዎች፡ ብቻ፡ ሣይሆን፡ በሠማያዊያን፡ መላዕክት፡ ዘንድም፡ በዓለመ፡ መላዕክት፡ ማህበር፡ መኖሩን፡ ይህም፡ ማህበር፡ በዘጠና፡ ዘጠኝ፡ ነገደ፡ መላዕክትና፡ በዘጠና፡ ዘጠኝ፡ የነገድ፡ አለቆች፡ የተከፋፈለና፡ የተመደበ፡ መሆኑን፡ መምህራንና፡ መጻህፍት፡ ይነግሩናል።

ማህበር፡ በማህበርተኞቹ፡ ከሚያከናዉኑት፡ ተግባራት፡ አንጻር፡ እንዲሁም፡ ይዘት፡ ከተነሳው፡ አላማ፡ አኳያ፡ ሲመዘን፡ ዓለማዊ፡ ወይም፡ መንፈሳዊ፡ማህበር፡ ሊባል፡ ይችላል። ዓለማዊ፡ ማህበር፡ በአንድ፡ ነገር፡ ላይ፡ አንድ፡ ዓይነት፡ ፍላጎት፡ ያላቸው፡ ሠዎች፡ ፍላጎታቸውን፡ ወይንም፡ ዓላማቸውን፡ ለማሳካት፡ በጋራ፡ የሚያከናውኑት፡ ተግባር፡ ነው። መንፈሳዊ፡ ማህበር፡ ብለን፡ የምንጠራው፡ ማህበር፡ ግን፡ በዓለም፡ ውስጥ፡ እየኖሩ፡ የዓለሙን፡ አታላይነት፡ እና፡ ሀላፊነት፡ ተገንዝቦ፡ በልክ፡ እየኖሩ፡ ነገረ፡ እግዚአብሔርን፡ በማሠብ፡ ትዕዛዛቱን፡ በመጠበቅ፡ ምዕመናትንና፡ ቤተክርስቲያንን፡ በማገልገል፡ ተስፋ፡ የምናደርጋትን፡ መንግስተ፡ ሠማያት፡ በጋራ፡ መውረስ፡ ነው።

በኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋህዶ፡ ቤተክርስቲያን፡ ውስጥ፡ መንፈሳዊ፡ ማህበራት፡ ተብለው፡ ከሚታወቁት፡ ወይም፡ ከሚጠሩት፡ አንዱ፡ እና፡ ዋነኛው፡ የጽዋ፡ ማህበር፡ ነው። የጽዋ፡ ማህበር፡ አበው፡ሊቃውንት፡ እንደሚሉት፡ ከሆነ፡ ረጅም፡ ዕድሜና፡ ከቤተክርስቲያኒቱ፡ ታሪክ፡ ጋር፡ የሚጋራ፡ ዕድሜ፡ ያለው፡ ነው፡ ይሉታል። የጽዋ፡ ማህበር፡ ሲቋቋም፡ ወይም፡ ሲመሠረት፡ መጠሪያ፡ ስም፡ ወይም፡ መታሰቢያ፡ ይኖረዋል።

1. ለምሳሌ፡ በጌታ፡ በራሱ፡ ዕለተ፡ ሰንበትን፡ ምክንያት፡ በማድረግ፡ ሰንበቴ፡ ተብሎ፡የጽዋ፡ ማህበር፡ ሊጠጣ፡ ይችላል። እንዲሁም፡ መድሃሊዓለም፤ በዓለወልድ፡ እና፡ ሌሎችንም፡ ሊጨምር፡ ይችላል።
2. በእመቤታችን፡ በቅድስት፡ ድንግል፡ማርያም፡ ሥም
3. በቅዱሳኑ፡ እና፡ በሠማዕታቱ፡ ሥም፡ እንዲሁም
4. በቅዱሳን፡ መላዕክቱ፡ ሥም፡ ማህበሩ፡ ሊሠየም፡ ይችላል።

የጽዋ፡ ማህበር፡ ወይም፡ የጸበል፡ ጸዲቅ፡ ዝግጅት፡ ዋናው፡ ዓላማው፡ እና፡ መነሻው “ በጻድቅ፡ ሥም፡ ንጹህ፡ ውሃ፡ ያጠጣ፡ የጻድቁን፡ ዋጋ፡ ይወስዳል” የሚለው፡ አምላካዊ፡ ቃል፡ ነው። ጌታችን፡ አምላካችንና፡ መድኃኒታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ የማዳን፡ መረቡን፡ ሲያሰፋ፡ እና፡ የሠው፡ ልጆች፡ በተለያዩ፡ መልኩ፡ መዳን፡ እንዲችሉ፡ ከላይ፡ በገለጽነው፡ መልኩ፡ ጸበል፡ ጸዲቅ፡ በሥማቸው፡ ለሚፈተትላቸው፡ ወዳጆቹ፡ የማዳን፡ወይም፡ የማማለድ፡ ቃል፡ኪዳን፡ ገብቶላቸዋል። ከዚህ፡ አንጻር፡ የእኛን፡ የመድኃኔአለምን፡ማህበር፡ ስንመለከተው፡ ከራሱ፡ ከፈጣሪ፡ ከተማላጅ፡ ቃል፡የተገባልን፡ መሆናችንን፡ እንረዳለን። በማህበራችን፡ ዙሪያ፡ የምናደርገው፡አገልግሎት፡ የምናቀርበው፡ ጸበል፡ ጸዲቅ፡ በምጽአት፡ ቀን፡ በፍርድ፡ አደባባይ፡ ብራብ፡ አብልታችሁኛልና፡ ብጠማ፡ አጠጥታችሁኛልና፡ እናንተ፡ የአባቴ፡ ቡሩካን፡ ወደ፡ እኔ፡ ኑ፡ የሚል፡ የተስፋ፡ ድምጽ፡ የሠነቀ፡ ነው። በዚህም፡ መሰረት፡ እኛም፡ ይህንኑ፡ ፈለግ፡ በመከተል፡ በመድሃኔአለም፡ ስም፡ የጽዋ፡ ማህበር፡ አቋቁመናል።

እግዚአብሔር፡ ማህበራችንን፡ ያስፋልን። አሜን!!!

# በደብረሰላም፡ መድኃኔዓለም፡ የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋህዶ፡ ቤተክርስቲያን

# የመድኃኔዓለም፡ የጽዋ፡ ማህበር መተዳደሪያ፡ ደንብ

# ሚኒሶታ

**አንቀጽ፡ 1. ስያሜና፡ አድራሻ**

1.1 የማኅበሩ፡ ስም "**የመድኃኔዓለም፡የጽዋ፡ማህበር** " (ከዚህ፡ በኋላ፡ "**ማህበሩ**") እየተባለ፡ ይጠራል።

1.2 የማህበሩ፡ አድራሻ፡

4401 Minnehaha Avenue South
Minneapolis, MN 55406

ሲሆን፡ ወደፊት፡ የአድራሻ፡ ለውጥ፡ ቢያስፈልግ፡ የደብረሰላም፡ መድኃኔዓለም፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋህዶ፡ ቤተክርስቲያንን፡ አድራሻ፡ ይከተላል

**አንቀጽ፡ 2. ዓላማ**

2.1 ከመድኃኔዓለም፡ ላገኘነው፡ ጸጋና፡ በረከት፡ በአንድነት፡ በመሆን፡ በጸበል፡ ጸዲቅ፡ ምስጋና፡ ማቅረብ፤

2.2 አቅም፡ በፈቀደ፡ ምግባረ፡ ሠናይ፡ ተግባሮችን፡ ለነዳያን፤ ለተቸገሩ፡ ቤተክርስቲያናት፤ እንዲሁም፡ ለትሩፋት፡ ድርጅቶች፡ ርዳት፡ ማድረግ፤

2.3 የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋህዶ፡ ሃይማኖትን፡ መጠበቅ፤ ማጠንከር፤ ለእድገትዋም፡ ያልተቆጠበ፡ ጥረት፡ ማድረግ፤

2.4 የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋህዶ፡ ሃይማኖት፡ ከትውልድ፡ ወደ፡ ትውልድ፡ እንዲሸጋገር፡ አስፈላጊውን፡ ማህበራዊ፡ አስተዋጽኦ፡ ማድረግ፤

2.5 "ብራብ፡ አብልታችሁኛል፤ ብጠማ፡ አጠጥታችሁኛል፤ ብታመም፡ ጠይቃችሁኛል፤ ብታሰር፡ አስፈትታችሁኛል፤ ብታረዝ፡ አልብሳችሁኛል? " የሚለውን፡ አምላካዊ፡ ቃል፡ ምርኩዝ፡ በማድረግ፡በአባል፡ /አባል፡ ቤተሰብ፡ ላይ፡ በሚደርሱ፡ ማህበራዊ፡ ችግሮች፡ ላይ፡ ንቁ፡ ተሳትፎ ፡ (መጠየቅ፤ ማጽናናት፤ እንዲሁም፡ እንደ፡ አስፈላጊነቱ፡ የእርዳታ፡ ልግስና)፡ ማድረግ፤

**አንቀጽ፡ 3. የአባልነት፡ መስፈርት**

3.1 ማንኛውም፡ ዕድሜው፡ ከ18 አመት፡ በላይ፡ የሆነ፡ የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋህዶ፡ ኃይማኖት፡ ዕምነት፡ ተከታይና፡ የደብረሰላም፡ መድኃኔአለም፡ ቤተክርስቲያን፡ ወቅታዊ፡ሙሉ፡ አባል፡ የሆነ፤

3.2 የመድኃኔአለም፡ የጽዋ፡ ማህበርን፡ ደንብና፡ መመሪያ፡ አክብሮ፡ በማስከበር፡ ለተግባራዊነቱም፡ የሚተጋ፤

3.3 የመድኃኔዓለም፡ የጽዋ፡ ማህበር፡ የስራ፡ አመራር፡ በደንቡ፡ መሰረት፡ የሚሰጠውን፡ ትዕዛዝና፡ መመሪያ፡ ለመፈጸም፡ ሙሉ፡ ፈቃደኛ፡ የሆነ፤

3.4 የጽዋ፡ ማህበሩን፡ በማንኛውም፡ የስራ፡ ዘርፍ፡ ለማገልገል፡ ፈቃደኛ፡ የሆነ፡ ሁሉ፡ የማህበሩ፡ አባል፡ መሆን፡ ይችላል።

## አንቀጽ፡ 4. መብትና፡ ግዴታ

4.1 መብት

ሀ. ማንኛውም፡ የማህበሩ፡ አባል፡ በአመራርና፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የስራ፡ ዘርፎች፡ ራሱንም፡ ሆነ፡ ሌሎችን፡ የመምረጥ፡ መብት፡ አለው።

ለ. ማንኛውም፡ አባል፡ ማህበሩ፡ በሚያዘጋጀው፡ ጉባኤና፡ የጸበል፡ ጸዲቅ፡ ዝክር፡ ላይ፡ የመሳተፍ፡ መብት፡ አለው።

ሐ. ባልና፡ ሚስት፡ የሆኑ፡ አባላት፡ ከላይ፡ በአንቀጽ 3፡ ንዑስ፡ አንቀጽ 3.1፡ የተጠቀሱትን፡ መስፈርቶች፡ ያሟሉ፡ ሆነው፡ ከተገኙ፡ ለወርኃዊ፡ ክፍያና፡ ለሌሎችም፡ መዋጮዎች፡ እንደ፡ አንድ፡ አባል፡ ሆነው፡ የሚቆጠሩ፡ ሲሆን፡ ሌሎች፡ መብቶቻቸው፡ ግን፡ እንደግል፡ የተጠበቁ፡ ይሆናሉ።

4.2 ግዴታ

ሀ. እያንዳንዱ፡ አባል፡/አባል፡ ቤተሰብ(ባለትዳር)፡ የማህበሩን፡ ደንብ፡ የማክበርና፡ የማስከበር፡ ግዴታ፡ አለበት።

ለ. እያንዳንዱ፡ አባል፡ እንዲሁም፡ አባል፡ ቤተሰብ( ባለትዳር)፡ ማህበሩ፡ የመደበውን፡ ወርኃዊ፡ መዋጮ፡ በወቅቱ፡ መክፈል፡ ይጠበቅበታል።

ሐ. እያንዳንዱ፡ አባል/ አባል፡ ቤተሰብ( ባለትዳር)፡ የማህበሩ፡ አመራር፡ በሚያወጣው፡መርሃ፡ ግብር፡ መሰረት፡ የጸበል፡ ጸዲቅ፡ ዝክር፡ ማዘጋጀት፡ ይጠበቅበታል።

መ. በመርሃ፡ ግብሩ፡ መሰረት፡ አዘጋጅ፡ ቤተሰብ፡ የማህበሩን፡ አባላትና፡እንግዶቹን፡ማስተናገድ፡ ይጠበቅበታል።

ሠ. ወርኃዊ፡ መዋጮም፡ ሆነ፡ የጸበል፡ ጸዲቅ፡ዝክር፡ በወቅቱ፡ ያልከፈለ፡ በመጀመሪያ፡ በአመራሩ፡ ማስጠንቀቂያ፡ ከተሰጠው፡ በኋላ፡ ካልታረመ፡ በዝክረ፡ ካህን፡ እንዲመከር፡ ሆኖ፡ለውጥ፡ ካላሳየ፡ ከማህበሩ፡ እስከመወገድ፡ ይደርሳል።

## አንቀጽ 5. ክፍያ

5.1 መደበኛ፡ መዋጮ

ከላይ፡ በአንቀጽ፡ 2፡ የተዘረዘሩትን፡ ምግባረ፡ ሠናይ፡ ተግባሮች፡ ለማከናወን፡ የገንዘብ፡ መዋጮ፡ አስፈላጊ፡ ስለሆነ፡ አባላት፡ በየወሩ፡ የ$3.00፡ወቅታዊ፡ መዋጮ፡ ማድረግ፡ ይጠበቅባቸዋል። ይህንኑም፡ እንደአመችነቱ፡ የ3 ወር፤ የ6 ወር፤ ወይም፡ የአመቱን፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ መክፈል፡ ለማህበሩ፡ ሥራ፡ ቅልጥፍና፡ ከፍተኛ፡ አስተዋጽኦ፡ ስለሚኖረው፡ የተጠቃለለ/ በከፊል፡ የተጠቃለለ፡ ክፍያ፡ እንዲኖር፡ ማህበሩ፡ ያበረታታል።

5.2 ልዩ፡ መዋጮ

ማህበሩ፡ አጣዳፊና፡አስቸኳይ፡ተግባሮችን፡ ለማከናወን፡ ከመደበኛው፡ክፍያ፡በተጨማሪ፡ ገንዘብ፡ ሲያስፈልገው፡ በአባላት፡ ፈቃድ፡ የሚወሰንና፡ በተመደበለት፡ የጊዜ፡ ሠሌዳ፡ የሚከፈል፡ መዋጮ፡ ሊጠይቅ፡ ይችላል። ልዩ፡ መዋጮ፡ ለመወሰን፡ የአባላት፡ ብዛት፡ ከጠቅላላው፡ አባላት፡ ከግማሽ፡ በላይ፡ መሆን፡ አለበት። በዚህም፡ የአብላጫ፡ ድምጽ፡ የተሰጠበት፡ ውሳኔ፡ የጸና፡ ይሆናል።

5.3 አስራት፡ በኩራት፡

በቤተክራስቲያን፡ ሥርዓት፡ መሰረት፡ እያንዳንዱ፡ የእምነት፡ ተከታይ፡ ከሚያገኘው፡ ማንኛውም፡ ገቢ፡ ላይ፡ አስራት፡ በኩራት፡ ማውጣት፡ ይጠበቅበታል። በሚልኪያ፡ ም 3 ቁ 10 እንደተጻፈው፡ “ በቤቴ፡ ውስጥ፡ መብል፡ እንዲሆን፡ አስራቱን፡ ሁሉ፡ ወደ፡ ጎተራ፡ አግቡ፤ የሰማይንም፡ መስኮት፡ ባልከፍትላችሁ፤ በረከትንም፡ አትረፍርፌ፡ ባላፈስስላችሁ፡ በዚሁ፡ ፈትኑኝ፡ ይላል፡ የሰራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር”፡ በሚለው፡ አምላካዊ፡ መርህ፡ መሰረት፡ እያንዳንዱ፡ አባል፡ ድርሻውን፡ በፖስታ፡ በማድረግ፡ በየወሩ፡ ለገንዘብ፡ ያዥ፡ ገቢ፡ ማድረግ፡ ይችላል።

## አንቀጽ፡ 6. ከአባልነት፡ ስለመወገድ

6.1 አንድ፡ አባል፡/ አባል፡ ቤተሰብ(ባለትዳር) ፡ የማህበሩን፡ ሕገ፡ ደንብ፡የተላለፈ፤ ያላከበረ፤ እንዲሁም፡ ግዴታውን፡ ለመወጣት፡ ያልቻለ፡ ከሆነ፡ በቅድሚያ፡ በአመራር፡ አካላት፡ የእርምት፡ ማስጠንቀቂያ፡ ተሰጥቶት፡ በተሰጠው፡ ጊዜ፡ ገደብ፡ ውስጥ፡ ካልተሻሻለ፡ እንዲሁም፡ በዝክር፡ ካህን፡ ምክር፡ ተሰጥቶት፡ ካልተለወጠ፡ ከማህበሩ፡ በይፋ፡ ይወገዳል።

6.2 አንድ፡ አባል/ አባል፡ቤተሰብ፡ በራሱ፡ ፈቃድ፡ ወይም፡ በጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ ወይም፡ በሥራ፡ አመራሩና፡ በዝክረ፡ ካህኑ፡ ውሳኔ፡ ከአባልነት፡ ከተወገደ፡ እስከዚያን፡ ጊዜ፡ ድረስ፡ ያዋጣው፡ መዋጮ፡ ወይንም፡ በማህበሩ፡ ስም፡ ከተቀመጠው፡ ገንዘብ፡ ምንም፡ ዓይነት፡ ክፍያ፡ መጠየቅ፡ አይችልም።

**አንቀጽ 7. የማህበሩ፡ ድርጅታዊ፡ መዋቅር፡ የሥራ፡ አመራር፡ ተግባርና፡ ኃላፊነት**

7.1 ድርጅታዊ፡ መዋቅር

ሀ. የማህበሩ፡ ጠቅላላ፡ ጉባኤ

ለ. የሥራ፡ አመራር፡ ኮሚቴ

7.2 የጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ ተግባርና፡ ኃላፊነት

ሀ. የማህበሩ፡ 50% + 1፡ አባላት፡ የተገኙበትና፡ ዓቢይ፡ ጉዳዮችን፡ ለመወሰን፡የሥራ፡ አመራሩ፡የጠራው፡ስብሰባ፡ የጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ ሥብሰባ፡ ይሆናል።

ለ. ጠቅላላ፡ ጉባኤው፡ የሥራ፡ አመራር፡ ኮሚቴ፡ አባላትን፡ ይሾማል፤ ይሽራል።

ሐ. ጠቅላላ፡ ጉባኤው፡ የሥራ፡ አመራር፡ ኮሚቴውን፡ ዓመታዊ/ ወቅታዊ፡ ሪፖርት፡ ያዳምጣል፤ ያጸድቃል፤ እንደአስፈላጊነቱም፡ ውሳኔ፡ ይሰጥበታል።

መ. መደበኛ፡ የጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ ስብሰባ፡ በአመቱ፡ መጨረሻ፡ በአመት፡ አንድ፡ ጊዜ፡ ይደረጋል። አስፈላጊ፡ ሆኖ፡ ሲገኝም፡ የሥራ፡ አመራሩ፡ ወቅታዊና፡ አጥዳፊ፡ ጉዳዮች፡ ሲያጋጥሙት፡ ልዩ፡ የጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ ስብሰባ፡ ሊጠራ፡ ይችላል።

ሠ. ለመደበኛም፡ ሆነ፡ ለልዩ፡ ጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ ስብሰባ፡ ግዴታቸውን፡ ካሟሉ፡ አባላት፡ መካከል፡50% + 1፡ በላይ፡ የሆኑት፡ ከተገኙ፡ ምልዓተ፡ ጉባኤ፡ ይሆናል።

ረ. ይህን፡ የማህበሩን፡ መተዳደሪያ፡ ደንብ፡ አንቀጾች፡ ለማሻሻል፡ ሲያስፈልግ፡ በምልዓተ፡ ጉባኤው፡ ከተገኙት፡ መካከል፡66 % እና፡ ከዚያ፡ በላይ፡ ድምጽ፡በመስጠት፡ ከደገፉት፡አንቀጹ/ አንቀጾቹ፡ ሊሻሻሉ፡ወይም፡ ሊሰረዙ፡ ይችላሉ።

ሸ. ማህበሩን፡ ለማፍረስ፡ በሚፈለግበት፡ ጊዜ፡ ግዴታቸውን፡ላጠናቀቁትና፡ ለዚሁ፡ ተብሎ፡ በተጠራው፡ ምልዓተ፡ ጉባኤ፡ በተገኙበት፡ የጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ አባላት፡ ከ75 % እና፡ በላይ፡ ሲደግፉ፡ብቻ፡ ማህበሩ፡ ሊፈርስ፡ ይችላል። በዚህን፡ ወቅት፡ በእጅ፡ ያለ፡ንብረትና፡ገንዘብ፡ለደብረሰላም፡መድኃኔአለም፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋህዶ፡ ቤተክርስቲያን፡ ገቢ፡ የሚደረግ፡ ሲሆን፡ ለአባላት፡ የሚከፋፈል፡ ወይም፡ የሚመለስ፡ ንብረትም፡ ሆነ፡ ገንዘብ፡ አይኖርም።

7.3 የሥራ፡ አመራር፡ ኮሚቴ

1. ሙሴ( ሊቀመንበር)
2. ም/ል ሙሴ (ጸሐፊ)
3. ገንዘብ፡ ያዥ

ሀ. ጠቅላላ

1. የሥራ፡ አመራር፡ ኮሚቴው፡ በጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ የተመረጡ፡ ከ3-5፡ አባላት፡ ይኖሩታል።

2. የሥራ፡ አመራሩ፡ የሥራ፡ ዘመን፡ 2 አመት፡ ይሆናል። ሆኖም፡ የስራ፡ አመራሩ፡ በአገልግሎቱ፡ እንዲቀጥል፡ ከተጠየቀና፡ የጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ ድጋፍ፡ ካገኘ፡ ለሁለተኛ፡ የሥራ፡ ዘመን፡ አገልግሎት፡ ሊሰጥ፡ ያችላል። ነገር፡ ግን፡ በአገልግሎቱ፡ ለመቀጠል፡ ፈቃደኛ፡ ያልሆነ፡ የሥራ፡ አመራር፡ አባል፡ ካለ፡ እንዲቀጥል፡ አይገደድም። በምትኩ፡ ሌላ፡ አባል፡ ሊመረጥ፡ ይችላል።

3. የሥራ፡ አመራሩ፡ የሥራ፡ ድልድል፡ በጠቅላላ፡ ጉባኤው፡ ይወሰናል።

4. የሥራ፡ አመራሩ፡ መደበኛ፡ ወይም፡ ልዩ፡ ጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ እንዲጠራ፡ በድምጽ፡ ብልጫ፡ ሲወሰን፡የጉባኤውን፡ ቀን፤ ቦታና፤ ሠዓት፡ ወስኖ፡ ለአባላት፡ ቢያንስ፡ ከአንድ፡ ወር፡ በፊት፡ ያስታውቃል።

5. ከአባላት፡ መካከል፡ 20% የሚሆኑ፡ አባላት፡ልዩ፡ የጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ እንዲጠራላቸው፡ ፔቲሽን፡ ሲያቀርቡ፡ ፔቲሽኑ፡ በቀረበ፡ በ30፡ ቀናት፡ ውስጥ፡ አመራሩ፡ ልዩ፡ የጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ መጥራት፡ አለበት። የ30 ቀኑ፡ የጊዜ፡ ገደብ፡ ካለፈ፡ ፔቲሽን፡ የፈረሙት፡ ስብሰባውን፡ የመጥራት፡ ሙብትና፡ በዚያ፡ ስብሰባ፡ ምልዓተ፡ ጉባኤ፡ መሙላቱ፡ ከተረጋገጠ፡ በጉባኤው፡ የሚወሰኑትን፡ ውሳኔዎች፡ አመራሩ፡ ተግባራዊ፡ የማድረግ፡ ግዴታ፡ አለበት።

6. ባልና፡ ሚስት፡ በአመራር፡ ውስጥ፡ በአንድነት፡ ሊያገለግሉ፡ አይችሉም።

ለ. የሥራ፡ አመራር፡ ኮሚቴ፡ ተግባርና፡ ኃላፊነት

1. የማህበሩን፡ ወርሃዊ፡ የጸበል፡ ጸዲቅ፡ ዝክር፡ መርሃ፡ ግብር፡ ያወጣል። ያሳውቃል። በወቅቱ፡ መፈጸሙንም፡ ያረጋግጣል።
2. ስብሰባዎችን፡ በዴሞክራሲያዊ፡ የስብሰባ፡ ደንብ፡ መሰረት፡ ይመራል።
3. የጸበል፡ ጸዲቅ፡ ዝግጅትና፡ መስተንግዶ፡ በሥርአት፡ መካሄዱን፡ ይመራል። ይቆጣጠራል።
4. የመዝሙር፡ አገልግሎት፡ በዝክሩ፡ ወቅት፡ እንዲከናወን፡ ይከታተላል። ያስተባብራል።
5. የማህበሩ፡ አባላት፡ በየዝክሩ፡ ቀን፡ መገኘታቸውን፡ ይቆጣጠራል። ባልተገኙት፡ላይ፡ በጽዋ፡ ማህበሩ፡ ሕገ፡ ደንብ፡ መሰረት፡ ተገቢውን፡ እርምጃ፡ ይወስዳል።

ሐ የሥራ፡ አመራር፡ ኃላፊዎች፡ ተግባርና፡ ኃላፊነት፡

1 ሙሴ (ሊቀመንበር)

1.1 የዝክር፡ ቀን፡ ፕሮግራሞችና፡ ስብሰባዎችን፡ በስርአት፡ ይመራል።
1.2 በተለያዩ፡ ስብሰባዎች፡ የሥራ፡ ግብዣዎችና፡ ማህበራዊ፡ ግንኙነቶች፡ ላይ፡ የጽዋ፡ ማሃበሩን፡ በመወከል፡ ይገኛል፡ ወይም፡ ሌሎች፡ እንዲወክሉት፡ ያደርጋል።
1.3 ከገንዘብ፡ ያዢው፡ ጋር፡ በመሆን፡ የማህበሩን፡ ሂሳብ/ ገንዘብ፡ ያንቀሳቅሳል።
1.4 ከማህበሩ፡ ወጪ፡ የሚሆኑ፡ ደብዳቤዎችና፡ ማስታወቂያዎች፡ ላይ፡ ፈርሞ፡ እንዲሰራጭ፡ ያደርጋል።

2 ም/ሙሴ( ጸሐፊ)

2.1 የስብሰባ፡ ቃለጉባኤዎችን፡ ይይዛል።

2.2 ከሙሴው፡ ጋር፡ በመነጋገርና፡ በሚሰጠው፡ መመሪያ፡ መሰረት፡ የስብሰባ፡ አጀንዳዎችን፡ ያዘጋጃል።

2.3 የማህበሩን፡ ፋይሎች፡ በሚገባ፡ ያደራጃል። የአባላትንም፡ ስምና፡ አድራሻ፡ በመዝገብ፡ ይይዛል።

2.4 ደብዳቤዎችን፡ አዘጋጅቶ፡ በሙሴው፡ ከተፈረመ፡ በኋላ፡ ወጪ፡ ያደርጋል።

2.5 በጸበል፡ ጸዲቅ፡ ዝክር፡ ቀን፡ ለዝግጅቱ፡ አስፈላጊ፡ የሆኑት፡ ቁሳቁስ፡ ጽዋ፤ድምጽ ማጉያ፤ጠረጴዛና፡ ወንበር፤ ከበሮ፡ መሚላታቸውን፡ ያስተባብራል። ይመራል። ይቆጣጠራል።

2.6 ሙሴው፡ በሌለበት፡ ጊዜ፡ እሱን፡ ተክቶ፡ ይሰራል።

3. ገንዘብ፡ ያዥ

3.1 ከአባላት፡ የሚሰበሰቡ፡ ክፍያዎች/ መዋጮዎችን፡ ይሰበስባል። በማህበሩ፡ የባንክ፡ ሂሳብ፡ ውስጥ፡ በ2 ቀናት፡ ጊዜ፡ ባንክ፡ ገቢ፡ ያደርጋል።

3.2 በሂሳብ፡ አያያዝ፡ ደንብ፡ መሰረት፡ የሂሳብ፡ መዛግብት፡ ያዘጋጃል፤ይመዘግባል፤ ባንክ፡ ካለው፡ ሂሳብ፡ ጋር፡ መመሳከሩንም፡ በየጊዜው፡ ይቆጣጠራል።

3.3 ማንኛውም፡ ወጪ/ ክፍያ፡ በቼክ፡ መሆኑን፡ ያረጋግጣል።

3.4 ከሙሴው፡( ሙሴው፡ ከሌለ፡ ከም/ል፡ ሙሴው፡ ) ጋር፡ በመሆን፡ ገንዘብ፡ ወጪ፡ ያደርጋል።

3.5 ለጥቃቅን፡ ወጪዎች፡ የተመደበውን፡(petty cash) ጥሬ፡ ገንዘብ፡ ይይዛል። በሙሴው፡ ሲፈቀድም፡ ወጪ፡ ያደርጋል። የወጪ፡ ሰነዶችንም፡ በማሰባሰብ፡ ምትክ፡ ገንዘብ፡ ከባንክ፡ እንዲተካለት፡ ያደርጋል።

3.6 የገንዘብ፡ ገቢና፡ ወጪ፡ ሪፖርት፡ በየ6 ወሩ፡ ለስራ፡ አመራር፡ ኮሚቴ፤ በየአመቱ፡ ለጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ ሪፖርት፡ ያቀርባል።

4. የቁጥጥር፡ ቡድን

4.1 እንደአስፈላጊነቱ፡ ሁለት፡ አባላት፡ ያሉት፡ የቁጥጥር፡ ቡድን፡ በጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ ይመረጣል። ተጠሪነቱም፡ ለጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ ይሆናል።

4.2 የጽዋ፡ ማህበሩን፡ የአስተዳደርና፡ ፋይናንስ፡ አያያዝ፡ በሕግ፡ ደንቡ፡ መሰረት፡ ትክክለኛ፡ መሆኑን፡ ይመረምራል፤ይቆጣጠራል። በጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ ስብሰባ፡ ላይም፡ ሪፖርት፡ ያቀርባል።

**አንቀጽ 8. <u>መተዳደሪያ፡ ደንቡ፡ የሚጸናበት፡ ጊዜ</u>**

ይህ፡ መተዳደሪያ፡ ደንብ፡በአባላት፡ ሙሉ፡ፈቃድና፡ ፊርማ፡ተረጋግጦ፡ ከህዳር፡ 28 ቀን 2007 ዓም/ December 7 2014፡ ጀምሮ፡ በሕግ፡ የጸና፡ ይሆኗል።